ኢ ሀ ሥ ኢ

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገሁዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ኅንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net

sh1@ttomar.net

ጥ_ኢ.-1_20120116_0

ልዩ ፡ ማስታወቂያ ።

ጥሪ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡—

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!

ለሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ ዐብር!

መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!

ከማንም ፡ በፊት ፥ በሥልጡንሕዝብናኽ ፥ "ኢትዮጵያ" ፡ የምትባል ፡ ቅድስት ፡ ሀገርኽን ፡ ከውነኽ ፥ በሀገራዊ ፡ እግዚእናኽ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ እየሠራኽና ፡ እያደስክ ፥ ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ባሕርያውያን ፡ መብቶችኽን ፡ እያስከበርክ ፥ እንሆ ፡ ለምእት ፡ ዓመታት ፥ በሐራ ፡ ሕዝብነትና ፡ በሐራ ፡ ሀገርነት ፡ ተከብረኽ ፡ ኖረኽባታል ።

በነዚህ ፡ ዘመናት ፡ የጥፋትና ፡ የጭቈና ፣ የውንብድናና ፡ የውርደት ፡ ወቅቶችም ፡ ተፈራርቀውብኻል ። ዅልጊዜም ፡ ቢኾን ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ መልሰኽ ፡ ያስከበርከውና ፥ ሀገርኽን ፡ መልሰኽ ፡ የዋጀኽው ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽን ፡ በሥልጣኔኽ ፣ በሥልጡንሕዝብናኽ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ አጽንተኽው ፡ በመታገልኽ ፡ ነበር ።

ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ በተለየ ፡ ኹኔታ ፥ ሰንደቅ ፡ ዐላማኽ ፡ ተዋርዶ ፥ እግዚእናኽ ፡ ተረምርሞ ፥ በገዛ ፡ ሀገርኽ ፡ "ባይተዋር" ፡ ተብለኽ ፥ ርስትኽን ፡ ተነጥቀኽ ፥ ባልፈቀድከው ፡ የ "አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ ላጰያፊ ፡ አመሳሶ ፣ ላሠቃቂ ፡ የመብት ፡ ጥሰትና ፡ ለውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ተዳርገኽ ፡ ትገኛለኽ ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ ከ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ አጋማሽ ፡ ወዲህ ፥ የለውጥ ፡ ምኞት ፡ ተዋሽቶልኽ ፡ ነበር ። ከዓመት ፡ ተኩል ፡ በኋላ ፥ ኹኔታው ፡ ሲገመገም ፥ ከተዋሸልኽ ፡ "ሥር ፡ ነቀል" ፡ ለውጥ ፡ ውስጥ ፡—

- ባንድ ፡ ወገን ፥ የቀድሞ ፡ እስረኞች ፡ በከፊል ፡ ሲፈቱ ፥ በሌላ ፡ ወገን ፥ "መብታችን ፡ ይከበር" ፡ ያሉ ፡ የሰብኣዊ ፡ መብት ፡ ተሟጋቾች ፡ "አሸባሪዎች" ፡ ተብለው ፡ ዛሬ ፡ ታስረዋል ፤
- "የመጻፍና ፡ የመናገር ፡ መብት" ፡ በዚያችው ፡ በዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ ሊደረገም ፡ ተቃርቧል ፤
- በውጭ ፡ የሚገኙ ፡ "ተፎካካሪዎች" ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ቢገቡም ፥ የታጠቁ ፡ ተገንጣዮች ፡ በእየ "ክልሉ" ፡ አናስደርስ ፡ ብለዋቸዋል ።

"ግንቡን ፡ እንናድ ፤ ድልድዩን ፡ እንገንባ" ፡ የሚለው ፡ የድለላ ፡ ቃልም ፡ ዛሬ ፡ ታጥፎ ፥ የጠላኽውን ፡ አገዛዝ ፡ በማሸጋገር ፣ ማእከላዊ ፡ መንግሥትን ፡ በማዳከም ፣ "ክልሎችን" ፡ በማጠናከር ፥

ከ"ሹሉ ፡ የከፉ ፡ ደግሞ ፥ በእየ "ክልሉ" ፡ የ "ዘር ፡ ማጽዳት" ፡ ዘመቻን ፡ ከመቼውም ፡ የባሰ ፡ በማጠናከር ፡ ተተክቷል ። "የሕግ ፡ የበላይነት" ፡ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ቀሩና ፡ ተጥሎ ፥ ገዳይና ፡ አስገዳይ ፡ አላንዳች ፡ ሥጋት ፡ የሚፈነጨበት ፥ ተገዳይና ፡ ተበዳይ ፡ ፍትሕን ፡ ያጡበት ፡ አሳዛኝና ፡ አሥጊ ፡ ኹኔታ ፡ ተፈጥሯል ።

የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፥ አንተው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነኽ! ሌላ ፡ ማንም ፡ የለም! ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ መሥራትና ፡ በወደድከው ፡ ዐዳር ፡ ማደር ፡ ለማንም ፡ አሳልፈኽ ፡ የማትሰጠው ፡ የተቀደሰ ፡ የእግዚእናኽ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡—

- *ተነሥ!*
- *ተደራጅ!*
- *ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽን ፡ አጽና!*
- *ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ ሥራ!*
- *ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥትኽን ፡ አቁም!*

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.) ፥ ይህኑ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማኽን ፡ እዳር ፡ ለማድረስ ፡ የተቋቋመ ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ ነውና ፥ ፈጥነኽ ፡ ዐብርለት!

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥

ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥

ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።

www.slttunhzb.net